# <u>የግንቦት 20   ሀያ ሁለተኛ ዓመት ክብረ በዓል በሎስአንጀለስ ተከበረ</u>

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባደረጉት መራራ ትግልና በከፈሉት ወደርየለሽ መስዋዕትነት አምባገነኑ የደርግ ሥርዓት የተገረሰሰበት የግንቦት 20 ሀያ ሁለተኛ ዓመት ክብረ በዓል በሎስአንጀለስ የኢፌዲሪ ቆ/ጄ/ጽ/ቤት ተከብርዋል። በክብረ በዓሉ ላይ 100 ያህል በሎስአንጀለስና በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ተሳትፈዋል። በበዓሉ ላይ ክቡር አምባሳደር ዘሪሁን ረታ በሎስአንጀለስ የኢፌድሪ ቆንስላ ጄኔራል ባደረጉት ንግግር ባለፉት 22 ዓመታት በአገራችን ስለተገኙ ዋና ዋና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታና የልማት ውጤት ገለፃ አድርገዋል።



( ክቡር አምባሳደር አቶ ዘሪሁን ረታ እና አቶ ኢሳያስ ጎታ መግለጫ ሲሰጡ)

አገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ማንነትዋን በሚያዋርድ የድህነትና መሀይምነት አረንቋ ውስጥ መቆየቷን፣ በግንቦት 20 ድል ግን የደርግ መንግስት ከተገረሰሰ በኃላ አስፈሪውን አገራዊ ሁኔታ ፈፅሞ ለመቀየር ባደረግነው ጥረትና ርብርብ ሚሊዮኖች ይራቡ የነበረበት ሀገር ሚሊዮኖች ራሳቸውን ከመመገብ አልፈው ለሌላውም ማምረትና ሀብት መፍጠር የሚችሉበት ደረጃ ለማድረስ የተቻለ መሆኑን፣ በርካታ የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎች እንደተከናውኑና ልማታዊ ባለሀብቶች በሀገር ውስጥም እየተፈጠሩ ከውጭም እየጎረፉ ባከናወኑት የኢንቨስትመንት ስራ ሀገሪቱ ተጨባጭ የልማት ማዕበል ውስጥ መግባቷን ገልፀዋል።

በማያያዝም ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ማርቀቅና ማፅደቅን ጨምሮ የምርጫ ህግ፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት፣ የፕሬስ ሕግ፣ የመደራጀት መብት፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ያለገደብ መከበሩና የዲሞክራሲያዊ ተቋማት እንዲገነቡ የተደረገው ጥረት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት

ለመገንባት ወሳኝ ክንውኖችና ውጤቶች መሆናቸውን አስምረውበታል። በተለይም የብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋና ባህላቸው የተከበረበት፣ በልዩነታቸውና ህብረ ብሔርነታቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑበት ስርዓት በፅኑ መሰረት መገንባት መጀመሩን አስታውቀዋል ።

በኢኮኖሚ ፖሊሲ ረገድም የግብርና መሪ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂን መንደፍዋን፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሀግብሮችንና የሴክተር ልማት ስትራቴጂዎችን ነድፋ ተግባራዊ ማድረጎን፣ የግሉን ሴክተር ተሳትፎ የሚያበረታታ የኢንቨስትመንት ሕግ ማውጣቷን፣ ልማት አጋዥ የሆነ የፊስካል እና የገንዘብ ፖሊሲዎችን ማውጣቷን፣ ግዙፍ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መሰረተ ልማት አውታሮች መዘርጋቷን ወዘተ... ገልፀዋል። በእነዚህና በተዛማች እርምጃዎች ምክንያት ኢኮኖሚው ከሚያሽቆለቁልበት ወደማንሰራራት መሸጋገሩን ብሎም ባለፉት 10 ተከታታይ ዓመታት 11% እድገት ማስመዝገቡን፣ በዚህም ድህነት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ መቻሉን ገልፀዋል።



(ከተሳታፊዎች መካከል በከፊል)

በዚህ ሂደት ለአገራችን ሕዳሴ ብስራት በፍፁም ታታሪነት ከፍተኛ ሕዝባዊ ፍቅር ሲረባረቡ የነበሩትን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ማጣታችን ከፍተኛ ሀዘን ሲሆን የዘንድሮ የግንቦት 20 በዓል በመለስ አስተምሮ የሕዳሴ ጉዞችን ይሳካል በሚል ህዝባችን በከፍተኛ ቁጭት እየተንቀሳቀሰ እንዳለ ገልፀዋል። በበዓሉ የተገኙት ታዳሚዎች በሰጡት አስተያየት፡-

" ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ በሁሉም አቅጣጫዎች ስር ነቀል ለውጥ በማስመዝገብ ወደፊት ጉዞ ላይ መሆንዋን እንደተገነዘቡ ፣

" በአንዳንድ አካባቢዎች ያሉ የዲያስፖራ አባላት በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረግ በስፋት በማሳተፍ ተጠቃሚ በመሆኑ ላይ እንደሚገኙ"፣ ሰሜን አሜሪካ ያለነው በዚህ ረገድ ወደኃላ ቀርተናል"፣

"እዚህ አገር የምንለፋውን ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነን ብንሰራ የት በደረስን?" ፣



(ተሳታፊዎች ጥያቄና አስተያየት ሲያቀርቡ)

"ታላላቅ የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵየያ መሳባቸው ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ያላትን አመቺነትና ለብልፅግና ያላትን ተስፋ ያሳያል"፣

"በኢትዮጵያ ውስጥ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በስፋት የማስተዋወቅ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል"፣



(ተሳታፊዎች ጥያቄና አስተያየት ሲያቀርቡ)

"ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ ቦንድ በመግዛት መረባረብ አለብን" ወዘተ.. የሚሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

በመጨረሻም ታዳሚዎች ዲሞክራሲያዊት፣ የበለፀገችና የሁላችንም የሆነችውን አዲሲቷን ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት እና ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ስኬታማነት የሚቻለውን ሁሉ አስተዋፅኦ ለማበርከት ቃል በመግባት ስብሰባውን አጠናቀዋል።